የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አስራ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፳፯
አዲስ አበባ ሚያዝያ ፲፮ ቀን ፪ሺ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No 27
ADDIS ABABA-24th April 2008

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፩፻፵፱/፪ሺ
የቃሊቲ ኮንስትራክሽንና የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ገጽ.. ፬ሺ፷፫

## CONTENTS

Regulation No .149/2008
Kality Construction and Construction Materials Production Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation ........................................ ..Page 4063

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፵፱/፪ሺ**

**የቃሊቲ ኮንስትራክሽንና የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯/፩ (ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የቃሊቲ ኮንስትራክሽንና የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፵፱/፪ሺ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. መቋቋም

፩. የቃሊቲ ኮንስትራክሽንና የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል ፡፡

፪. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል ፡፡

፫. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

የሃገር መከላከያ ሚኒስቴር የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል ፡፡

Council Of Ministers Regulation No. 149/2008

*COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF KALITY CONSTRUCTION AND CONSTRUCTION MATERIALS PRODUCTION ENTERPRISE*

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article-47 (1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/19992.

1. *Short Title*

This Regulation may be cited as the "Kality Construction and Construction Materials Production Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No. 149/2008".

2. *Establishment*

1) The Kality Construction and Construction Materials Production Enterprise (hereinafter the "Enterprise") is hereby established as a public enterprise.

2) The Enterprise shall be governed by the public Enterprise Proclamation No. 25/1992.

3. *Supervising Authority*

The Ministry of National Defense shall be the supervising authority of the Enterprise.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
P.O.Box 80001

፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ቦታዎች ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ሊኖሩት ይችላል ፡፡

፭. ዓላማ

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው ፤

፩. የመከላከያን የግንባታ ፍላጐት ለማሟላት ማናቸውም የህንፃና የመኖሪያ ቤቶች ኮንስትራክሽን ሥራ ማካሄድ ፤

፪. በተጓዳኝ በአገሪቱ በሚከናወኑት ማናቸውም የህንፃ ግንባታ ሥራዎች መሣተፍ ፤

፫. ለመከላከያ የኮንስትራክሽን ሥራዎች የሚያገለግሉ የጠቅላላ ብረታ ብረት ሥራዎችንና የእንጨት ምርት ውጤቶች የኮንክሪትና ሌሎች የኮንስትራክሽን ዕቃ ዎች ማምረትና ፤ በተጓዳኝ ለገበያ ማቅረብ እና

፬. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ማናቸውንም ሌላ የንግድ ሥራ መሥራት

፮. ካፒታል

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፬፻ ሚሊዮን (አራት መቶ ሚሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥም ብር ፪፻፭ ሚሊዮን ፭፻፳፮ሺ ፯፻፶፮ (ሁለት መቶ አምስት ሚሊ ዮን አምስት መቶ ሃያ ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ስድስት ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል ፡፡

፯. ኃላፊነት

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም ፡፡

፰. ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል ፡፡

፱. የተሻረ ደንብ

የቃሊቲ ኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፭/፲፱፻፺፰ በዚህ ደንብ ተሽሯል ፡፡

፲. የመብትና ግዴታ መተላለፍ

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፭/፲፱፻፺፰ ተቋቁሞ የነበረው የቃሊቲ ኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፈዋል ፡፡

፲፩. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ፡፡

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፲፮ ቀን ፪ሺ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

4. *Head Office*

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

5. *Purposes*

*The Purposes for which the Enterprise is established are:*

1) to engage in building construction activity mainly to satisfy the national defense construction needs,

2) in parallel, to engage in other building construction works,

3) to engage in the production and supply of metal and wooden products, concrete and other construction materials for defense construction and others, and

4) to engage in any other business conducive to the attainment of its purpose.

6. *Capital*

The authorized capital of the Enterprise shall be Birr 400,000,000 (Four Hundred Million) of which Birr 205,526,756 (Two Hundred five Million five Hundred Twenty Six Thousand Seven Hundred Fifty Six Birr) is paid up in cash and in kind.

7. *Liability*

The Enterprise shall not be liable beyond its total assets.

8. *Duration*

The Enterprise is established for an indefinite duration.

9. *Repeal*

The Kality Construction Materials Production Enterprise Establishment council of Ministers Regulation No. 45/1998 is hereby repealed.

10. *Transfer of right and obligation*

The rights and obligations of Kality Construction Materials Production Enterprise established under the council of Ministers Regulation No. 45/1998 are hereby transferred to the enterprise.

11. *Effective Date*

This Regulation shall enter into force upon the date of publication in the Federal Negarit Gazeta

*Done at Addis Ababa, this 24th. Day of April, 2008.*

*MELES ZENAWI*

*PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*